# መመርያዎች



## የተመዘገቡ መራጮች በአካል ሳይገኙ እንዴት ሊመርጡ እንደሚችሉ

**የሚያስፈልጎት ነገሮች**

- የምርጫ ካርድ*
- ቡናዊ ቀለም ያለው ፖስታ*
- ነጭ የሲግኔቸር ፖስታ*
- ተለቅ ያለ ነጭ የሚመለስበት ፖስታ*

*ከእነዚህ ውስጥ ኣንዱ እንኳን ከጎደለ፡ የቀበሌዎን ኣስመራጭ ኮሚቴ ባለስልጣኖችን ያነጋግሩ።

- ጥቁር ቀለም ያለበት ብዕር
- የመታወቅያ ወረቀት ካርድ ቁጥር፡
  የሚኖሶታ መንጃ ፍቃድ ቁጥር፡ የሚኖሶታ የመታወቅያ ካርድ ቁጥር፡ ወይም የሶሺያል ሴኩሪቲ (Social Security) ካርዶ የመጨረሻዎቹ ኣራት ቁጥሮች።
  *ከእነዚህ ቁጥሮች ኣንዱም ከሌሎት፡ ዝቅ ብለው ይመልከቱ*
- ምስክር
  ማንኛውም በሚኖሶታ ለመምረጥ የተመዘገበ ሰው፡
  *ባለቤትዎ ወይም ዘመድዎ ጭምር ሊሆኑ ይችላሉ።*
  ወይም ህጋዊነት ያለው የህዝብ መታወቅያ
  የሚያረጋግጥ ኣካል ወይም መሃላ ለማስፈጸም ህጋዊነት ያለው ሰው




❶ ይምረጡ!

- ባዶ የምርጫ ወረቀትዎን ለምስክሮቹ ካሳዩ በውሃላ ለብቻዎ ሁነው ምርጫዎ ላይ ምልክት ያድርጉ።
- በምርጫ ወረቀቱ ላይ ያሉትን መመርያዎች ተከተሉ።
- በምርጫው ወረቀት ላይ ስሞንም ሆነ የመታወቅያ ወረቀት ቁጥሮን በምንም ቦታ ላይ <u>ኣይጻፉ።</u>
- ከተፈቀደው ቁጥር በላይ ዕጩዎችን <u>ኣትምረጡ</u>። ይህንን ካደረጉ በዛ ምርጫ ጣብያ ውስጥ የመረጡዋቸው ሁሉ ተቀባይነት ኣያገኝም።
  *በምርጫ ወረቀትዎ ላይ ስህተት ካደረጉ ፡ ከምርጫ ወረቀቱ በስተጀርባ ተመልከቱ።*




❷ የምርጫ ወረቀትዎን ቡናዊ ቀለም ባለው ፖስታ ውስጥ ከተው ያሽጉ

- በዚህ ፖስታ ላይ ምንም ነገር ኣትጻፉ

❸ ቡናዊ ቀለም ያለውን ፖስታ በነጩ ሲግኔቸር ፖስታ ውስጥ ይክተቱት




❹ ነጩን የስግኔቸር ፖስታ <u>ሙሉ በሙሉ</u> ይምሉት።

- ምልክት ከሌለው፡ ስሞንና የሚኖሶታ ኣድራሻዎን ይጻፉ።
- የሚኖሶታ የመንጃ ፍቃድዎን ቁጥር፡ የሚኖሶታ መታወቅያ ወረቀትዎን ቁጥር፡ ወይም የሶሻል ሴኩሪቲ (Social Security) የመጨረሻዎቹን ኣራት ቁጥሮች ይጻፉ።
  እነኚህ ያስገብዋቸው ቁጥሮች፡ በኣካል ተገኝተው ለማይመርጡና ከእለቱ በፊት ለሚመርጡ ሰዎች የሚሰጥ የምርጫ ወረቀት እንዲሰጥዎት ባስገቡት ማመልከቻ ላይ ያሰፈሩዋቸው ቁጥሮች ጋር ኣንድ ዓይነት መሆናቸውን ያረጋግጡ ።
  እነዚህ ቁጥሮች ከሌሎት፡ ሳጥኑ ላይ ምልክት ያድርጉ።
- ቃለ መሃላውን ኣንብበው ይፈርሙ።
- ምስክርዎ ስማቸውን እንዲያሰፍሩ፡ የሚኖሶታ የከተማ ኣድራሻቸውን እንዲሁም የሚኖሩበትን ከተማ (የፖ.ሳ>ቁ ሳይሆን)በዝርዝር እንዲጽፉ በመጨረሻም ፊርማቸውን እንዲያሰፍሩ ጠይቁ።
  *ምስክሮ ባለስልጣን ወይም የታወቀ ህጋዊ ኣካል ከሆኑ፡ ከኣድራሻ ይልቅ ስልጣናቸውን ማስፈር ኣለባቸው። በህግ የታወቀ ኣካል ከሆነ ደግሞ ማህተማቸውን ማስፈር ኣለባቸው።*
- ፖስታውን ያሽጉ







❺ የግል መረጃዎችዎ እንዳይታዩ፡ ከሚታዩበት ኣቅጣጫ ገለል ያድረጉ፡ የሲግኔቸር ፓስታውን በትልቁ የመመለሽያ ነጭ ፖስታ ውስጥ ይክተቱ።

- ፖስታውን ያሽጉ

❻ የምርጫ ወረቀትዎን፡ <u>በመመለሻው ፖስታ ላይ ወደ ተጻፈው ኣድራሻ፡ምርጫ በሚደረግበት ቀን እንዲደርስ ይላኩ ።</u>
የምርጫ ወረቀትዎ ወደ ምርጫ ጣብያው ላይደርስ ይችላል።
ይህ እንዳይሆን ሶስት ኣማራጮች ኣሎት፡

- ወረቀትዎ ምርጫ በሚካሄድበት ዕለት እንዲደርስልዎ፡ የሚፈጅበትን ቀን በደንብ ኣጥንተው በዩ ኤስ ፖስታቤት ይላኩ።
- የምርጫው ቀን ከመድረሱ በፊት ወይም በምርጫው ዕለት ከቀኑ ዘጠኝ ሰዓት በፊት በኣካል ሂደው ይስጡ።
- ሌላ ሰው፡ በምርጫው ዕለት ከዘጠኝ ሰዓት በፊት ሂዶ እንዲሰጥሎት ይጠይቁ።
  ይህ የሚልኩት ሰው ከሶስት የምርጫ ወረቀቶች በላይሊያስረክብ ኣይችልም።




የኣካል ስንክልና ካሎት ከዚህ ጽሁፍ በስተጀርባ በመመልከት ልዩ መመሪያዎችን ማየት ይችላሉ።

የዚህ በኣካል ሳይገኙ ያካሄዱት የምርጫ ውጤት ምን እንደሆነ ለማየት **www.mnvotes.org**ን ይጎብኙ።

## ስህተተን ማረም




- በቂ ግዜ ካሎት፡ የምርጫ ኮሚቴው ኣዲስ የምርጫ ወረቀት እንዲልክሎ ይጠይቁ ወይም
- በስህተት ምልከት ያደረጉበትን የዕጩውን ስም በደንብ ኣድርገው ይሰርዙት። ከዛ በውሃላ በሚመርጡት ሰው ስም ላይ ምልክት ያድርጉ። (ባደረጉት እርማት ላይ የስሞን ኣህጽረ- ቃል ኣታስፍሩ)።

---

## የኣካል ጉድለት ካለቦ

የኣካል ጉድለት ካለቦ ወይም ምርጫዎ ላይ ምልክት ለማድረግ የማይችሉ ከሆነ፡ ምስክሮ፡ እርስዎ በሚሰጡት መመርያ መሰረት ምርጫዎ ላይ ምልክት በማድረግ፡ ማንኛውንም ነገሮች በማሰባሰብና ፎርሞችን በመሙላት ሊተባበርዎ ይችላል።

በምርጫው ፖስታ ላይ ሲፈርሙ፡ የሚኖሶታ ህግ እንደሚከተለው ማድረግ ኣለቦት ይላል፡

- ወደ ምርጫ ጣብያ የሚላከውን ወረቀት መፈረም ያለቦት ራስዎ ኖት ወይም
- ምልክት ማድረግ ያለቦት ራስዎ ኖት ወይም
- እርስዎ ራስዎ ባሉበት፡ ምስክሮ እንዲፈርምልዎ መጠየቅ ይችላሉ (ምስክሩ የራሱንም ስም ጭምር መፈረም ኣለበት)።
- ፊርማዎ ያለበት ማህተም ካሎት ፡ እሱን መጠቀም ይችላሉ ወይም ምስክሮን እርስዎ ባሉበት ማህተሞን ተጠቅሞ ፊርማዎን እንዲያስቀምጥሎት ይጠይቁ።

የሚኖሶታ ህገ-መንግስት፡ ክፍል 645.44፡ ክፍል 14

በደንብ ይመልከቱ፡ በውክልና ድምጽ መስጠት ኣይቻልም። ከላይ እንደተጠቀሰው።ከላይ እንደተጠቀሰው፡ ውክልና የተሰጠው ሰው፡ በእርስዎ ፊት ሊፈርምልዎ ብቻ ነው የሚችለው።

---

የሚስጥራዊነት ማስታወቅያ፡ የምርጫ ወረቀትዎ ተቀባይነት ካገኘ፡ ስሞና ኣድራሻዎ፡ ምርጫንና ፖለቲካን በሚመለከት፡ ለህጋዊ ጉዳዮች ጠቀሜታ ለህዝብ ክፍት ይሆና። ከዚህ በስተቀረ፡ በምርጫ ወረቀትዎ ላይ ያስቀመጡት መረጃ ሁሉ ለኣስመራጭ ኮሚቴው ባለስልጣኖች ብቻ በምርጫው ቀን እስከ ምሽቱ ሁለት ሰዓት ድረስ ብቻ ክፍት ሆኖ ይቆያል። ከዛ በውሃላ የምርጫው ወረቀትዎና በላዩ ላይ ያለው መረጃ ሁሉ(ከመታወቅያ ወረቀት ቁጥሮ በስተቀር) ለህዝብ ክፍት ይሆናል።የመታወቅያ ወረቀትዎ ቁጥር የሚያስፈልግበት ምክንያት በኣካል ተገኝቼ ለመምረጥ ኣልቻልምና የምርጫ ወረቀት ላኩልኝ ብሎ ማማልከቻ ያስገባው ሰው እርስዎ መሆንዎንና ኣለመሆኖን ለማረጋገጥ ነው። ኣልሰጥም ለማለት ይችላሉ። ግን የምርጫ ወረቀትዎ ተቀባይነት ላያገኝ ይችላል። በተጨማሪም የምርጫ ወረቀትዎ ምን ላይ እንደደረሰ ከመከታተል ይታገዳሉ ማለት ነው።